**ቀን፡ ነሐሴ 19/ 2007 (25/08/2015)**

## በስመ አብ፤ ወወልድ፤ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሀዱ አምላክ፤ አሜን!!

## ውድ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ሆይ።

**እናስተውል፡** *ሃሰት ነገሰ፤ ዳቢሎስ ነገሰ ነው። ሃሰትን መዋጋት ደግሞ ዲያብሎስን መዋጋት ነው።*

ክርስቶስ በደሙ የዋጀን እኛ ክርስቲያኖችና ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሃሰትና ቅጥፈት የሚናኝበት እየሆንን ነውና ይህንን ክርስቲያናዊ ያልሆነ ከፋፋይ የሃጢአት ሥራ ለማስቆምና ለማስወገድ የምንጥር እንጂ የሃስትና የቅጥፈት መሣሪያ በመሆን ከክርስቲያን ወገኖቻችን ጋር የምንናቆር አንሁን።

ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ሕዝብን ከሕዝብ የሚከፋፍልና የሚያናቁር ሃሰትና የቅጥፈት ስራ ብቻ መሆንኑን ሁሉም ይረዳ። ሃስትና ቅጥፈትን የደገፈና የተከተለ ክርስቲያን ሁሉ ከሃሰተኞቹና ከቀጣፊዎቹ ያነሰ ሃሰተኛና ኀጢዓተኛ ሊሆን እንደማይችል በሚገባ ሊረዳው ይገባናል።

አዕምሮውን የሰይጣን ማደሪያ ካላደረገና የሰው ልጅ ጤና ካልነሳው በስተቀር ውሸትንና ቅጥፈትን መተዳደሪያዬ ብሎ ሊይዝ አይችልም።

በተለይም ደግሞ፤ በፈጣሪው አምኖ በክርስትና የተጠመቀና እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ከሃሰትና ከውሸት ሁሉ ይርቃል እንጂ ከውሸትና ከቅጥፈት ጋር የሙጥኝ ብሎ ተጣብቆ አይቀርም፤ ምክንያቱም ውሸትና ቅጥፈት የክርስትና ሳይሆን የሰይጣንና የዲያቢሎስ መንገድ ነውና።

ወላጅ ለልጁ ቢዋሽ ነውር፤ አፀያፊና ከፉ ሃጢዓት እንደሆነ ሁሉ በተለይ ደግሞ አስተማሪ፤ የሀይማኖት አባትና መሪ የሆነ ካህን እውነትም ሕይወትም መንገድም የሆነውን የክርስቶስን መስቀል ተሸክሞ ከቶ ሊዋሽና ሊቀጥፍ አይገባውም።

ክህነትን ይዞ መዋሸትና መቅጠፍ የክርስትና ሳይሆን የሰይጣንና የዲያቢሎስ ስለሆነ ይህን ዓይነቱን ሰው ከተቻለ ሊያርሙት ካልሆነም ሊሸሹትና ሊያስወግዱት ይገባል።

*(አእምሮአቸውም በጠፋባቸው እውነትንም በተቀሙ እግዚአብሔርን መምሰል ማትረፊያ የሚሆን በመሰላቸው ሰዎች ይገኛሉ።እንደነዚሀ ካሉት ራቅ።1ኛ ጢሞቲ.6፤4-6።)*

እነዚህ ውሸትና ቅጥፈትን ኑሮአቸው ያደረጉ በተለይም ደግሞ አንዳንድ ካህናት የጌታ ቃሉን እያወቁ የሰውን ልጅ ብቻ ሳይሆን ልብና ኩላሊትን መርምሮ የሚያውቀውን ፈጣሪ አምላክን ሳይቀር ሳይፈሩ በማን አለብኝነት የሚዋሹና የሚቀጥፉ በመሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ የክርስትናው እምነት ራሱ አላቸው ብሎ መቀበል ያዳግታል።

ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለተፈጠረው ችግር ዋንኛው ጠንቅ ይኸው ውሸትና ቅጥፈት ነው። በተለይ ጥቂት ካህናትና ተከታዮቻቸው ከመሬት ተነስተው አይኑን ያፈጠጠና ጥርሱን ያገጠጠ ውሸት ለሕዝብ ያሰራጫሉ። አንደኛው ውሸታቸው ሲጋለጥ ደግሞ ሌላ ውሸትን በማፍለቅ ሃሰትን ይነዛሉ፤ እሱ ሲታወቅ ደግሞ ሌላ ተጨማሪ ውሸትን ለሕዝብ በማቅረብ በዚህ የውሸት ማዕበል ምክንያት ከተከፋፈለው ጎራ ከአንደኛው ወገን ጋር በመቆም ችግሩና ክፍፍሉ ሳያቋርጥ እንዲቀጥል በእሳት ላይ ነዳጅ እየጨመሩ እሳቱን በማጋጋም መቃቃሩን እያፋፋሙና እያቀጣጠሉ ይኖራሉ።

አንዳንድ ካህናት ለአስር፤ ሃያና ከዛም በላይ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክፉና በደጉ አብረውት የኖሩትን፤ ያቆረቡትን፤ ያጠመቁትንና በተክሊል የዳሩትን ከዚህም አልፎ የንሰሃ ልጆቻቸውን ሳይቀር ለስልጣንና ለግል ጥቅም ሲሉ አናውቃቸውም፤ የቤተ ክርስቲያኗም አባላት አይደሉም፤ በቤተ ክርስቲያኗም ላይ ምንም ዓይነት መብት የላቸውም በማለት በሕግ አደባባይ ሳይቀር ካዷቸው።

በምትኩም ለያዙት ዓላማ ይረዱናል ያሏቸውን ስለ ቤተ ክርስቲያኗም ሆነ ስለ አባላቷ ምንም የማያውቁ በአብዛኛው በወጣት የተሞሉ አዳዲስ ሰዎችን ከየቦታው በማሰባሰብ መላዕክት የመሰላችሁና ቤተ ክርስቲያንን ለማዳን የመጣችሁ በሚል የሃሰት ስብከትና ሙገሳ በቤተ ክርስቲያኗ አባላት ላይ እንዲዘምቱና ጥቃት እንዲፈጽሙ ለወንጀል ጋበዟቸው።

እነዚህ ለዓመታት አብረዋቸው የኖሩትን ካህናትና ምእመናን በአንድ ጀንበር ከድተው በጠላትነት የፈረጁ ካህናት ዛሬ በሃሰት ስብከት ያሰባሰቧቸው ሰዎች ነገ የእነሱን የግል ዓላማ ለማሳካት እንቅፋት ይሆኑናል ብለው ካሰቡ ሰው መሆናቸውንም አናውቅም ብለው ሊክዷቸው እንደሚችሉ አጠራጣሪ አይሆንም።

ይህን ድርጊት ፈጻሚ ዲያቆን ብቻ እንዳይባል፤ ከቄሱ፤ በቄሱ ብቻ ደግሞ እንዳያበቃ መነኩሴው፤ በዛም እንዳይቆም ከሊቀ ጳጳስ ውስጥም ሳይቀር የእውነቱን መንገድ ስተው የሃሰትን ጎዳና በመከተል ሕዝብን ለማሳሳት ሲሞክሩ እየተስተዋሉ ነው።

***(አወይ ትዝብት....*** *ሁሉን የምታይና የምትሰማ ፈጣሪ አምላከማ ከቶ ስንቱን ታዝበህ ይሆን? ስንቱንስ ታገስህ ይሆን?)*

*(የትዕግሥት አምላክ ሆንክ እንጂ መቸም እንደ አናንያ በደልና ስራ መዓትና እበሳ ወርዶብን ከዚች ከባረካትና ከቀደሰካት ምድር ብን ብለን መጥፋት በተገባን ነበር።)*

የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በእንግሊዝ ሃገር በለንደን ከተማ የመሠረቷትና ያደራጇት በርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላለፉት 3 ዓመታት ሕዝብን ከፋፍሎና አቃቅሮ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁከትና ብጥብጥን በማስነሳት የሥልጣንና የንዋይ ህልምን ለማሳካት ሲባል ከተነዙ ሃሰቶችና ከደረሰው ሁኔታ ውስጥ የተወሰኑትን እስቲ ለአብነት መለስ ብለን እንይ።

***<u>ውሸትና ቅጥፈት መጀመሪያውና መጨረሻው</u>***

1) **ቤተ ክርስቲያንን ቦርድ ሊያደርጓት ነው!!**
   *ይህ መዓት መጣብህ በሚል አይነት ከጥቂት ካህናት አንደበት እየወጣ የተነዛው ወሬ ሃሰትነቱ ያልገባቸው ወገኖች ቦርድ ማለት ምን ማለት ነው ብሎ ከመረዳት ይልቅ ቤተ ክርስቲያን ቦርድ አትሆንም ብለው በመነሳት ቦርድ የሚለው ቃል መለያያና መናቆሪያ ሆነ ። ከጊዜ ብዛት ግን ሰው በረጋ መንፈስ ሆኖ ሲረዳው ቦርድ ማለት ኮሚቴ ከማለት ያልዘለለ እንደሆነ በስፋት ማወቅ ሲጀምር ጉዳዩ ከንቱ ሆኖ ቀረ።*
2) **ቤተ ክርስቲያኗን ካምፓኒ ሊያደርጓት ነው የሚል የሃሰት ወሬ ተነዛ።**
   - *ካምፓኒ ከሆነች ካምፓኒ የተባለው አካል መጥቶ መቅደስ ውስጥ በመግባት ታቦቱን ነክቼ ልየው ይላል፤*
   - *ቁርባኑን ሆነ ሁሉንም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያናትን ሁሉ እኔ ካላየሁ ይላል፤*
   - *ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እኔ ባልኩት ይመራ ይላል*
   - *ቤተ ክርስቲያኗ በኑፋቄያውያን ትሞላለች*
   - *ቤተ ክርስቲያኗ ንግድ ቤት ትሆናለች*
   - *ቤተ ክርስቲያኗ የግለሰቦች ንብረት ትሆናለች ወ.ዘ.ተ.. ተባለ።*

   *ይህ የተባለው ቤተ ክርስቲያኗ በሕግ ፊት ሕጋዊ ሰውነት ስለሌላትና ንብረቷ በሰዎች ስም ተይዞ ስለሚገኝ ሕጋዊ ሰውነት ኖሯት በስሟ ንብረት መያዝ የምትችለው በCharitable Company limited by guarantee በመመዝገብ ስለሆነ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የቤተ ክርስቲያኗ አባላት ተወያይተው የሚያጸድቁት የመተዳደሪያ ረቂቅ ሲቀርብ ነበር።*

   *የቻሪቴብል ካምፓኒ መቋቋም ጉዳይ ለቤተ ክርስቲያኗ የሚያስገኘው ዘለቄታዊ ጥቅም ካለው ይጸድቃል፤ ከሌለው ደግሞ ተገምግሞ ይቀርና ሌላ አማራጭ ይወሰዳል፤ በዚህ ላይ መነጋገርና መከራከር ሲቻል በምትኩ ግን ሆነ ተብሎና ካህናት ስለሆንን የሃይማኖት ሕግ ሊፈርስ ነው ብለን ሕዝቡን ብናስበረግገው ያምነናል በሚል ሰይጣናዊ አስተሳሰብ በመመራት በሬ ወለደ ሃሰትን በማኾንዶንድ ያልተረዳው ሕዝብ እንዲበረግግና እርስ በእርሱ እንዲቃረን አደረጉ።*

   *ይህንን የሰማና ሃሰቱንና ቅጥፈቱን እውነት አድርጎ የተቀበለ ሁሉ በቀረበለት የተቀነባበረ የሃሰት ፈረስ ተሳፍሮ መጋለብና መጋለብ ጀመረ። አዎ እነዛ እውነታውን በትክክል እየተረዱ ነገር ግን ሆነ ብለው ሕዝብን በሃሰት አሳስተው የሚያናክሱ ጥቂት ካህናት እኩይ ድርጊታቸው ሰምሮ አንዱ ወገን በሌላው ላይ መነሳቱን እያዩ በሕዝብ መቃቂያል እያሾፉ ፈነጠዙ። ዛሬ ላይ ግን ያ ሁሉ ውሸትና ቅጥፈት እንጂ አንዳችም እውነት እንዳልነበረው ግልጽ ሆነ።*

3) **በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ልዩ ዓይነት ሲሲ ቲቪ ማስተከልና ለጸሎት የሚመጣውን ሕዝብ በቪዲዮ እየቀረጹ ማስፈራራት።**

በዕለተ ማርያም በቀኗ አባ ግርማ ከበደና ቄስ ዳዊት የተባሉ ካህናት CCTV ተካይ ካምፓኒ በመኮናተር የቤተ ክርስቲያኗን ግቢ ጉድጓድ ሲያስቆፍሩ ተስተዋሉ። በመጀመሪያ ለጸሎትና ለምስጋና ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጣን ክርስቲያን ለመሰለል ልዩ የሆነ የመሰለያ CCTV ማስጠመድ አስፈላጊ አይደለም ከተፈለገም ያለው ይበቃ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ በእንግሊዝ ሃገር የData protection ሕግ መሠረት አስፈላጊውን የሕግ መስፈርቶች ሳያሟሉ ከመሬት ተነስቶ የሕዝብን ምስል እየቀረጹ መያዝ ሕገ ወጥና የሰውን መብት የሚጥስ ተግባር ነው።

እነ ውሸት ካባው ግን ሕጋዊ ፍቃድ አለን፤ CCTV የመትከልና ክርስቲያኑን ሕዝብ የመከታተል መብትም አለን የሚል የተለመደው የሃሰት መረጃ ለሕዝብ በማስተላለፍ ይህንን ሃሰት ያልተረዱ ተከታዮቻቸው የወገኖቻቸውን ሰብዓዊ መብት መጣስ ደገፈው እንዲቆሙ አደረጉ።

እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል እንዲሉ የአካባቢው ባለሥልጣን (Council) ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የተተከለው CCTV ባስቸኳይ እንዲነሳ መመሪያ ሲሰጥ ዋሾዎቹ አመራሮች ግን ማስጠንቀቂያ እንዳልተሰጣቸውና ድርጊቱ ሕጋዊ መሆኑን የሚገልጸውን ውሸታቸውን በመንዛት ቀጠሉበት።

በመጨረሻም የአካባቢው ባለሥልጣን ሲሲ ቲቪውን መንግሎ በመጣል ከአካባቢው እንዲነሳ አደረገ። በዛን ወቅት የሚታይ የሚጨበጥ ተግባር በመሆኑ ለመዋሸት የማይቻል ቢሆንም አሁንም ግን ዋሾዎቹ ካውንስሉ ያነሳው በሕገ ወጥ መንገድ ነው በማለት ካውንስሉን ሕገ ወጥ አድርገው ለማቅረብ ሞከሩ።

የሕገ ወጥ ሥራው መዘዝ በዚህ አላለቀም እነሆ በአሁኑ ወቅት እነሱ እንቢ በማለታቸው ምክንያት ካውንስሉ ሲሲ ቲቪውን ያስወገደበትን £5.000.00 (አምስት ሺህ ፓውንድ) እንዲከፍሉ ካውንስሉ አዟቸዋል።

ይህ ከደረሳቸው ወራት ቢያልፉትም ከውሸት በስተቀር እውነትን የማይደፍሩት ሰዎች አሁንም ጉዳዩ ከሕዝብ ደብቀውት ይገኛሉ። ምክንያቱም እውነቱ ከተናገሩ ጥፋቱ የእነሱ በመሆኑ ክፈሉ እንዳይባሉና ዕዳውን የሕዝቡ ለማድረግ ነው።

4) **ውሸት በእንግሊዝ ከፍተኛው ፍርድ ቤት።**

- ሃይማኖታቸውንና የቤተ ክርስቲያን አባልነት መብታቸውን በማስከበር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሕግና ሥርዓትን ለማስፈን የተንቀሳቀሱት ካህናትና ምእመናን የፍትሕ ጥያቄአቸው በውስጥም ሆነ በውጪ ሽምግልና እንዲሁም በቻሪቲ ኮሚሽን በኩል በተደረገ ጥረት መፍትሔ ማግኘት ባለመቻሉ ጉዳያቸውን ወደ ሃገሪቱ የፍትሕ አካል በመውሰድ ለእንግሊዝ ከፍተኛው ፍርድ ቤት አቀረቡ።

  ይህንኑ ጉዳይ ተመልክቶ ብይን ለመስጠት አንድ ቀን ይበቃዋል የተባለ የፍርድ ቤት ሂደት አራት ቀን ፈጀ። ይህ ሁሉ ጊዜ የተወሰደውም የመናገር መብትን በመጠቀም ዋሾዎቹ ካህናት ረጃጅም ዲስኩሮችን በማቅረብ ብዙ ውሸቶችን በመናገር እውነትን ጋርደን ይፈረድልናል ብለው በመጣራቸው ሲሆን ከዛም በላይ ደግም ጠበቃቸው ሆኖ የቀረበው ሰው ከጥብቅና ሥነ ምግባር ይልቅ የዘመኑ የዘር የፖለቲካ ካድሬ ሆኖ በመቅረብ ከጉዳዩ ጋር የማይገናኝ ዝባዝንኬ ነገር ሳይቀር በመዘብዘብ የፍርድ ቤቱን ሰዓት በከንቱ በማባከኑ ነበር።

  የፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ብይን ከመሰማቱ በፊትም በተለይ የዋሾዎቹ ጠበቃ የፍርድ ቤቱን ሂደት ለ4 ቀናት ለመራዘም ምክንያት በመሆኑ በዚህ ተግባሩ ታላቅ ጀብዱ እንደፈጸመ ተደርጎ በዋሾዎቹ ካህናት ተነገረለት፤ ነገር ግን ሚሊዮን ውሸት አንዲትን ጥፍጥሬ የምታክል እውነት ጨፍልቆ ሊያጠፉ አይችልምና የቀረበው የፍትሕ ጥያቄ እውነትን የያዘ ጉዳይ ስለነበር ፍርድ ቤቱ ለእውነት ፈረደ።

- የፍርድ ቤቱ ብይን እንደተሰማም በዋሾዎቹ ይግባኝ ቀርቦ በዳኛው ውድቅ ሲደረግ ነገር ግን ለከፍተኛ የይግባኝ ስሚ ፍርድ ቤት (Court of appeal ) ይግባኝ የማሰማት መብትን ግን እንደማይከለክል የታወቀ ነበር። ሆኖም ግን የመጀመሪያው የይግባኝ አቤቱታ ውድቅ በመደረጉ የከፍተኛው የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትን መጠየቅ የሚቻለው ይግባኝ የማለት ፍቃድን (Permission to appeal ) ነበር።

- ዋሾዎቹና ቀጣፊዎቹ ካህናት ግን በተለመደው የቅጥፈት ምላሳቸው ለጉዳዩ የሃሰት ሽፋን በማበጀት የሃይማኖትና የቀኖና ቤተ ክርስቲያን ሕግ ተጣሰ የሚል ሽፋን በመስጠት ለከፍተኛው የይግባኝ ፍርድ ቤት በብይኑ ላይ ይግባኝ መጠየቃቸውንና ይግባኙም እሲኪሰማ የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ (Court order) የመፈጸም ግዴታ እንደሌለባቸው አይኑን ያፈጠጠና ጥርሱን ያገጠጠ ውሸት በመዋሸት በየአደባባዩ ሳይቀር ይሄንኑ የሃሰት መረጃ አሰራጩ።

ከዚህም ውስጥ የፍርድ ውሳኔውን ተቃውመው በእንግሊዝ ፍትሕ ሚኒስቴር መስሪያ ፊት ለፊት የዋሾዎቹ ተከታዮች ባደረጉት ሰላማዊ ሰልፍ ላይ እግዚአብሔርን ሳይፈሩና ሕዝብንም ሳያፍሩ ይግባኝ መጠየቃቸውንና ይግባኛቸውም ተቀባይነት እንዳገኘ ለሕዝቡ በይፋ ተናገሩ፤ በአደባባይ ለፈፉ።

እዚህ ላይ የሚገርመው የመጀመሪያው የፍርድ ቤት ትዕዛዝ የቤተ ክርስቲያኑ ቁልፍ አንድ ኮፒ ሕዝብ ለመረጣቸው ካህን እንዲሰጥና ሃሰተኞች በተንኮል ለሁለት እንዲከፈል ያደረጉት ሕዝብ በየተራ እንዲገለገል ነበር።

ነገር ግን ሃሰተኞቹና እብሪተኞቹ ቁልፉን ኮፒ አድርገን አንሰጥም በማለት የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ በማናናቅ ሊያልፉት ሞከሩ፤ ሆኖም ግን ማንም ሰው ከሕግ በላይ ሊሆን የማይችልበት የሕግ ሥርዓት ያለበት ሃገር ስለሆነ እብሪተኞቹ በሕገወጥ ድርጊታቸው ተመልሰው ፍርድ ቤት ቀረቡ።

እውነታው እነሱ ከሚያሰራጩት ሃሰትና ቅጥፈት ተቃራኒ በመሆኑም የፍርድ ቤትን ትዕዛዝ በመጣስ (Contempt of court) ተከሰው ለCommittal hearing በመቅረብ ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው ለእስር ሊዳረጉ ሲሉ እነሱ በጠላትነት ከሚፈሩጁቸው ክርስቲያን ወገኖቻቸው ምህረትን በማግኘት ከእሥር ተርፈው የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ተፈጻሚ ሊሆን ችሏል።

ይህ ብቻ አይደለም ጥፋተኞቹ የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ አናከብርም በማለታቸው በድጋሜ ተከሰው የቀረቡበትን ለCommittal hearing ሌላው አካል ያወጣውን ወጪ ከግላቸው እንዲከፍሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ወስኖባቸዋል። ይህ በግላቸው እንዲከፍሉ የተወሰነባቸው ክፍያም እስከ £50.000.00 (ሃምሳ ሺህ ፓውንድ) የሚደርስ ነው።

የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ተፈጻሚ የሆነውም ሕገወጦቹ እብሪተኞች የቁልፉን ኮፒ አድርገን አንሰጥም በማለታቸው የተነሳ የቤተ ክርስቲያኑ በሮች ቁልፍ በአዲስ እንዲቀየር ተደርጎ ነበር።

ለቤተ ክርስቲያኑ ቁልፍ መቀየር ምክንያቶቹ እነዚህ ሕግን አናከብርም ያሉ እብሪተኞች ሆነው ነገር ግን በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መሠረት የቤተ ክርስቲያኑ በሮች ቁልፍ ሲቀየሩ ዋሾዎቹ ተመልሰው የቤተ ክርስቲያን ቁልፍ አሰበሩ በማለት ሌላውን ወገን ጥፋተኛ አድርጎ ለማሳየትና በሕዝቡ መካከል ያለው መቃረን ወደ ከፋ ደረጃ እንዲሸጋገር ጣሩ፡፡

**አሁንስ ይህ ሕዝብን ያሞኙበት የይግባኝ ጥያቄአቸው ምን ላይ ደርሷል?**

በእነሱ ዘንድ ይግባኝ ጠይቀናል የሚለው ውሸታቸው ሳያቆም እንደቀጠለ ሲሆን ነገር ግን ከፍተኛው የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት (Court of appeal ) የጠየቁትን የይግባኝ መጠየቅ ፍቃድ (Permission to appeal) በJuly 23/2015 ውድቅ አድርጎታል። ለዚህ ገና ውሸት ስላልሰሩለት ሊሆን ይችላል እስከ አሁን ከተከታዮቻቸው ደብቀውት ይገኛል።

5) **በሃሰት ሽፋን ዋሾዎቹ የእንግሊዝን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይን ለማስቀልበስ ያደረጉት አሳፋሪና አሳዛኝ ተግባር።**

ሕዝብን በሃሰትና በቅጥፈት አስተባብሮ በማሰለፍና የሃሰት ፒቲሽን በማስፈረም በዕለተ ሰንበት የእንግሊዝ ፍትሕ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ፊትለፊት ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ።

አቡነ እንጦስ የተባሉት ጳጳስም ልብሰ ተክህኖ ለብሰው የፍትሕ አካሉን በሚቃወመው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ዋንኛ ተዋናኝ ሆኑ።

አቡነ እንጦስ ከሰላማዊ ሰልፉ በፊት በፍርድ ቤቱ ሂደትም ጸሎቱንና መንፈሳዊ አገልግሎቱን እርግፍ አድርገው ትተው ልክ እንደጠበቃ የዋሾዎቹን ወገን ደግፈው ከፍተኛው ፍርድ ይሙላለሱ ነበር።

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ግን ዋሾዎቹ ጳጳስ ያስከትሉ አያስከትሉ ሕዝብን በሚያሳስቱበትና በሚያናክሱበት የውሸት መዓት ሊደለልም ሆነ እውነትን ከማየት ሊከለል የሚችል አልነበረምና ጥረታቸው ከንቱ ነበር።

ይህ ሃሰተኛ የሃይማኖት ሽፋን በመስጠት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ለማስቀልበስ የተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ የተሰለፈውን ሕዝብ ቀርቶ ሌላውንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ሳይቅር ሊያሳፍር የሚችል ኋላ ቀር ተግባር ከመሆን ያለፈ ነገር ሳያመጣ እንዲሁ መና ሆኖ ቀረ፡፡

6) **የአቡነ እንጦስ በሕግ አስከባሪዎች ከእንግሊዝ ሃገር ተዋርደው መባረር።**

አቡነ እንጦስ ሕገ ወጥ ተግባርን በመፈጸም ሂትሮ የተባለው አየር ማረፊያ በእንግሊዝ ፖሊስ ቁጥጥር ሥር ውለው ከታሰሩ በኋላ በ72 ሰዓት ውስጥ ከእንግሊዝ ሃገር መባረራቸው በሕጋዊ ሰነድ ተረጋግጦ እያለ ነገር ግን ውሸታሞቹ አቡነ እንጦስ ሲኖዶሱ ለሥራ ጉዳይ ጠርቷቸው ሄዱ እንጂ አልተባረሩም በማለት የተለመደው ቅጥፈታቸውን አሰራጩ፤ ይኸው እስከ አሁንም ድረስ ከነሃሰታቸው አፋቸውን ይዘው ይኖራሉ።

7) **የወሲብ ጥቃት ክስና መጨረሻው**

አንድ ካህን የወሲብ ጥቃት አደረሰብኝ በሚል ክስ ያቀረቡ ምእመን ጉዳይ ሲጀመር ጀምሮ ጉዳዩ በውስጥ ሽምግልናና ይቅርታ እልባት እንዲያገኝ ከማድረግ ይልቅ በውሸት ለማድበስበስ ሲሞከር ጉዳዩ ወደ ፖሊስና

ከዛም ወደ ፍርድ ቤት በመድረስ ካህኑ ፍርድ ቤት ቀርበው እንዲፈረድባቸውና የሃይማኖታችንም ሆነ የቤተ ክርስቲያናችን ገበና ተጋልጦ በእንግሊዝ ጋዜጦች ላይ እንዲወጣ ተደረገ።

ከፍርዱ በኋላ ደግም ምእመኗ የቤተ ክርስቲያኗ ትረስቲ ነን በማለት ስማቸውን በቻሪቲ ኮሚሽን ዌብ ሳይት በመለጠፍ መሬት ጠበበን ያሉትን ትረስቲ ነን ባዮች 4 ካህናትና 5 ምእመናንን በግላቸው በመክሰስ የካሳ ጥያቄ ሲያቀርቡ እነዚህ ከሃሰት በስተቀር የእውነት ተግባር የማይሆንላቸው ሰዎች ሌላው ቀርቶ ፍርድ ቤት ቀረበው መከራከር ሲገባችው በተለመደው የእብሪትና ኋላ ቀር አስተሳሰባቸው ተገፍፍተው የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ በመናቅ ሳይቀርቡ ቀሩ።

አንዴም ብቻ ሳይሆን ለሁለተኛ ጊዜ ፍርድ ቤቱ እንዲቀርቡ ማዘዣ ልኮላቸው ለሁለት ተከታታይ ጊዜ ከፍርድ ቤት በመቅረታቸው ፍርድ ቤቱ ተከሳሾቹ በሌሉበት ጉዳዩን በማየት ወደ £80.000 የሚጠጋ የገንዘብ ካሳ በግላቸው እንዲከፍሉ ሊፈረድባቸው ችሏል።

በዚህ የፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረትም ዘጠኙ ሰዎች የተፈረደባቸውን ገንዘብ እንዲከፍሉ ሲጠየቁ እነሆ በአሁኑ ወቅት ደግሞ የቤተ ክርስቲያኗን ንብረት ተጠቅመው ገንዘቡን እንዲከፍሉ ይፈቀድላቸው ዘንድ በጠበቃቸው አማካኝነት ለሚመለከተው አካል በማመልከት ላይ ይገኛሉ።

እዚህ ላይ መረዳት የሚያስፈልገው የሰዎቹ ጥያቄ የተፈረደባቸውን ገንዘብ ለመክፈል የቤተ ክርስቲያኗን ንብረት ተጠቅመን ማለታቸው ህንፃ ቤተ ክርስቲያኑን ጭምር በወለድ አገድ አሲዞም ሆነ ሸጦ እስከመክፈል የሚደርስ ተግባር ለመፈጸም በመንቀሳቀስ ላይ መሆናችውን ነው።

8) **የአባ ግርማ ከበደ ከስልጣን መልቀቅና በምትካቸው ሌላ መሾም መወራት።**

አባ ግርማ በሕዝብ ውሳኔና ምርጫ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ተብለው የተሾሙ ሲሆን የአገልግሎት ዘመናቸው አልፎ ከሥልጣን አልወርድም በማለታቸው በ2012 ዓ/ም ያው የመረጧቸውና የሾማቸው የቤተ ክርስቲያኑ አባላት ከአስተዳዳሪነት አውርደዋቸዋል፤ በሥልጣናቸውም ላይ የሉም።

በርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን የመተዳደሪያ ሕግም ሆነ እስከ አሁን ሲደረግ የቆየው የቤተ ክርስቲያኑ አባላት መርጠው አስተዳዳሪ ይሾማሉ እንጂ ከአዲስ አበባ አስተዳዳሪ ተሹሞ አይላክላቸውም።

ወሬውም ከወሬነት አልፎ በአንዳችም የሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ ነገር ስለሌለው ከተለመደው ቅጥፈት የዘለለ አንዳችም የተጨበጠ እውነታ የለውምና በዚህ ሕዝብ ሊሞኝና ሊወናበድ አይገባውም።

9) **ቅዱስ ሲኖዶስ እና ሃገረ ስብከት**

በለንደን ደብረ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር ሲፈጠር ያለውን ችግር ፈትቶ ወደነበሩብት ሰላምና አንድነት መመለስ ሲቻል በችግሩ መካከል፤ ተነስቶ የማያውቀውን ጉዳይ የሲኖዶስ እና የሃገረ ስብከት ጥያቄ መጣ። አባ ግርማና ተከታዮቻቸው ከዚህ ዕለት ጀምሮ በሃገረ ስብከቱ ሥር ነን፤ በሲኖዶሱ ሥር ነን በማለት አዋጅ አሰሙ።

ቀጥሎም ከኢትዮጵያ የመጡ ጳጳሳት የተፈጠረውን ችግር መርምረው እውነትና ሃሰቱን አጥርተው በማየት የተናጋውን ሰላም ለማስታረቅ ከመሞከር ይልቅ ልክ ዓለማውያንና የፖለቲካ ልውካን እንደሚፈጽሙት ተግባር ጎራ ለይተው አንዱን በአንዱ አዝምቶ በመርታት ሥራ ላይ ብቻ ተጠመዱ።

ለዚህም ተግባራቸው ዋንኛ ምሥክር የሚሆነው ለሁለት ከተከፈለው ሕዝብ መካከል በአስተዳደር ላይ አለሁ የሚለውን የዋሾዎቹን ጎራ ካልሆነ በሥተቀር ፍትሕን የሚጠይቀውን አብዛኛውን የቤተ ክርስቲያኑን አባል እንደ መንፈሳዊ አባትነት ሄደን እንኳ እንባርከው ብለው ድፍረቱ ሳይኖራቸው ከአንዱ ወገን ጋር ብቻ ተጣብቀው፤ አንዱን ወገን ደግፈውና በአንደኛው ወገን መሃል ተደብቀው በመኖር ወደ መጡበት ተመልሰው መሄዳቸው ነበር።

ጳጳሳቱ ካከናወኑት ተግባር ውስጥም ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደረውን የምትመራው በካህናቱና በምእመኑ ሕብረት ነው የሚለውን ሕገ ቤተ ክርስቲያን ወደጎን በመተው ምእመኑ ዓይንም ሆነ አዕምሮ ሳይኖረው በካህናት ብቻ የሚመራና የሚነዳ ነው በሚል ፍጹም የተሳሳተ አስተሳሰብ በመመራት ካህናትን እየጠሩ በሃገረ ስብከቱ ሥር ነን፤ ኢትዮጵያ ባለው ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር ነን ብለው ፊርማ እንዲፈርሙ ማድረጋቸው ነበር።

በዚህ ከሃይማኖት አባቶች የማይጠበቅ ድርጊታቸው ምእመኑን በከፍተኛ ደረጃ ስላስቆጡት በአጸፋው የማይገባ ስድብና ውርደት ደረሰባቸው።

ያከናወኑትም አግባብነት የሌለው ተግባር የተወሰነውን ካህን ከመያዝና ታዛዣቸው ከማድረግ ያለፈ ብዙሃኑንና ዋልታና ምሶሶ ለሆነው ምእመን የፈየደው አንዳችም ነገር ስለሌለ የተፈጠረውን ችግር አባባሰው እንጂ አላረገበውም።

እነዚሁ ሲኖዶስን እንወክላለን የሚሉ ጳጳሳት አሁንም ካለፈው ስህተታቸው ሳይታረሙ እንደውም ባለፈው ፍትሕ ጠያቂው ሕዝብ አዋርዶናል የሚለውን ቂም ይዘው ወደ ለንደን በመምጣት አባ ግርማ ተነስተዋል፤ ሌላ አስተዳዳሪ ተሹሟል በማለት አንዳችም የሰነድ ማስረጃ የሌለው ወሬና አሉባልታ ለሕዝብ እንዲነዛ በማድረግ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።
ጉዳዩ ግን አሁንም እንዳለ ሆኖ የመጨረሻውን የፍርድ ቤት ውሳኔ ቀን ይጠብቃል እንጂ ፍትሕን ለማዛባትና የሰዎችን የሙብትና የፍትሕ ጥያቄ በሃሰትና አሉባልታ መቀልበስ ቀርቶ ማስቀምም አልተቻልም፤ አይቻልምም።

**10) ቤተ ክርስቲያንና ታቦት ረከሰ??**

ቄስ ብርሃኑ ብሥራት በለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከ22 ዓመታት በላይ ያገለገሉና ከ22 ዓመት በፊትም በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ አንድና ብቸኛ ቄስ የነበሩ ናቸው።
ሆነ ተብሎና ተቀነባብሮ በሕዝብ መካከል በተነዛው ሃሰትና ቅፈት ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈል ሲመጣ ክፍፍሉን በማጥበብ አንድ ለማድረግ የሚቻላቸውን ሁሉ ከጣሩ በኋላ አንድነትን ለማምጣት እንደሳቸው የሚጥር አቻ ካህን ማግኘት ተስኗቸው ጥረታቸው ሲከሽፍ እውነት አለበት ከሚሉት ወገን ጋር በመቆም መንፈሳዊ አገልግሎትን ብቻ በመስጠት የክህነት ተግባራችውን ተግተው ማከናወን ቀጠሉ።
ሆነ ተብሎና በተቀነባበረ ሁኔታ እሳቸውን በማስፈራራትና ካልተሳካም ክህነታቸውን በማገድ ለሙብቱና ለቤት ርክስቲያን ሕግ መከበር የፍትሕ ጥያቄ ያቀረበውን ሕዝብ እንረታለን ብለው ያሴሩት አቡነ እንጦስና አባ ግርማ ከበደ ቄስ ብርሃኑን በማስፈራራትና በማስጠንቀቅ ከሕዝብ መነጠል ሲሳናቸው አቡነ እንጦስ የቄስ ብርሃኑን ቅስና አግጃለሁ የሚል መግለጫ እንዲያወጡ ተደረገ።
በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት አንድ ካህን ክህነቱን ለመያዝና ለማውገዝ ምክንያቱም ሆነ አፈጻጸሙ ሥርዓትና ደንብ አለው።
በመጀመሪያ ደረጃ ቄስ ብርሃኑ ሰው ገድለው፤ ወይም አቁስለው በወንጀል አልተከሰሱም፤ ወይም ወንጀለኛ አልሆኑም፤ አልሰረቁም፤ የዝሙት ወንጀል አልፈጸሙም፤ ወይም ደግሞ የሃይማኖት ጥሰት አልፈጸሙም።
ይህንን ሁሉም ሆነ አንዱን ቢያደርጉም በመጀመሪያ ጉዳዩ ይጣራል፤ በማስረጃ ይረጋገጣል፤ ከዛም በማስጠንቀቂያ፤ በቅጣት፤ በመጨረሻም ክህነትን ለመያዝም ሆነ ውግዘት ደረጃ ይደረሳል።
እግዚአብሔር ያሳያችሁ፤ ቄስ ብርሃኑ ከመንፈሳዊ አገልግሎታቸው ውጪ በተነሳው ውዝግብ ውስጥ ገብተው እንኳ አንዱን ኮንነው ሌላውን አወድሰው ሲናጋሩና እንደ አንዳንዶቹ ካህናት ሲዛለፉ፤ ሲዋሹና ሲቀጥፉ ተደምጠው አያውቁም።
የእሳቸው ሃጢአትና በደል ተደርጎ የታየው ግን ለምን የፍትሕ ጥያቄ ላነሳው ሕዝብ መንፈሳዊ አገልግሎት ትሰጣለህ ነው።
ይህንን አቡነ እንጦስና አባግርማም ሆኖ ተከታዮቻቸው ልቦናቸው ያውቀዋል፤ የሚገርመው ግን የአቡነ እንጦስ የቄስ ብርሃኑን ክህነት ማገድ ደብዳቤ ይፋ እንደተደረገ ለዓመታት አብረዋቸው ያገለገሉና የኖሩ ነገር ግን ከሕዝብና ከቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት ይልቅ ለግል ሥልጣንና ጥቅም የቋመጡ ካህናት ምንም ሌላ ሙያና መተዳደሪያ የሌላቸውን አብዛኛው ዕድሜአቸውን ከክህነት ውጪ ምንም ነገር የማያውቁትን ቄስ ብርሃኑን ሳይውል ሳያድሩ ተሽቀዳድመው አቶ ብለው በመጥራት ለማዋረድና ለማቃለል መረባረባቸው ነው።
ቄስ ብርሃኑ ግን እንኳንስ በዚህ ሊጎዱና ሊሸማቀቁ ቀርቶ እንደውም የተዋጣላቸው የሃዋርያቱ ምሳሌ የሕዝብ ካህን ሆነው በእውነተኛ ሥራቸው ገፉበት።
በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉም ከእንግሊዝ ፍርድ ቤት በተሰጠው ብይን መሠረት ሕዝቡ በመረጠው ካህን የመገልገል ሙብት ስለተጎናጸፈ ሕዝቡም ቄስ ብርሃኑን አስቀድሞ በመምረጡ የቤተ ክርስቲያኑ ቁልፍ አንዱ ኮፒ ለእሳቸው እንዲሰጥ ተደረገ።
ከዚህ በኋላ ቄስ ብርሃኑ ለእውነትና ለፍትሕ የሚታገለውን ሕዝበ ክርስቲያን ለማገልገል ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ዋሾዎቹ ካህናት ቄስ ብርሃኑ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብተው ከቀደሱ ቤተ ክርስቲያኑና ታቦተ ጽላቱ ስለሚረክስ እኛ ገብተን መጸለይ የለብንም በሚል የፈጠራ አዋጅ በማወጅ እንደተለመደው ተከታዮቻቸው ማቂያቃል ጀመሩ። ይህም የፈጠራ ፕሮፓጋንዳቸውም እንደ እውነተኛ የሃይማኖት ሕግ ተቆጥሮ በዕለተ ሰንበትና በትንሳኤ ሌሊት ሳይቀር ተከታዮቻቸው በብርድ ተቆራምደው ከቤት ክርስቲያን ውጪ ግቢ ውስጥና በድንኳን ውስጥ እንዲጸልዩ አስደረጉ።
ቀጥለውም ቄስ ብርሃኑ ከቀደሱበት በኋላ በጳጳስ እየተባረከ ነው የምንገባው በማለት ሕዝበ ክርስቲያኑን መቀለጃ እያደረጉት ቆዩ።

**አሁንስ??**

ከያዝነው ወር ጀምሮ ጳጳሳቱ ሁሉ ጥለዋቸው ሲሄዱ ምንም ምንም ሳይሉ ያንን የነዙትን ቅጥፈት ሁሉ እርግፍ አድርገው ትተው ቅዳሜ ዕለት እውነተኛ የሕዝብ ካህን የሆኑት ቄስ ብርሃኑ ቀድሰው እነሱ ደግሞ በማግስቱ እሑድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰተት በለው በመግባት እየተገለገሉ ይገኛሉ።

ሁሉም መረዳት የሚገባው የእነዚህ ጥቂት ካህናት በሃይማኖትና በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ሽፋን የሚነዙት የሃሰትና የቅጥፈት መዓት ዓላማው አንደኛውን ልዩ አማኝ፣ ሌላውን ደግም የማያምን፣ አስመስሎ በማሳየት በሕዝብ መቃቃር ለማትረፍና በዛ ልዩነት ተጠቃሚ ሆነው ለመኖር ብቻ ነው።

**እናስተውል..** ከክርስትናው አልፎ የክርስቶስንና የሃዋርያቱ ምሳሌ መሆን የሚገባው ካህን የተጣላን የሚያስታርቅ፣ ለሕዝብ ሰላም አንድነትና መፈቃቀር በጉልበቱ ተንበርክኮ ፈጣሪን የሚለምን መሆን ሲገባው ኩቶ እንዴት ቢሆን ነው ሕዝብን ከሕዝብ በሚያነጣጥልና ሕዝብን በሕዝብ ላይ በሚያነሳሳ ተግባር የሚጠመደው?

***ይህንን መሰሉን ተግባር የሚፈጽምስ ክህነት ቀርቶ ክርስቲያንስ ብሎ ማመን ይቻላል?***

ልብ ያለው ልብ ይበል!!

ቸሩ መድሐኒዓለም ክፍና ደጉን ለይተን ለማወቅ የሚያስችል ልቦና ይስጠን!!

ሰላም፣ ፍቅርና አንድነታችንን ይመልስልን፣ አሜን።

አሰፋ ምንተስኖት